# ውሽልሽል

*(ከእኔ- ዓለም)*

ውሽልሽል ውትፍትፍ የተለጣጠፈ፣
ትርጉም የለሽ ኅብረት ያልተደጋገፈ፣
በወግ ያልተመነዠከ የልተገረደፈ፣
በኢትዮጵያዊነት ለእውነት ያልቆመ ሁሉን ያላቀፈ፣
ለአገር የማያስብ በወገን ለሥልጣን እየተጣደፈ፣
ውሸት በክህደት ላይ ከመጠን ባለፈ፣
ድርጅት ነን፣ ውህደት በተወታተፈ፣
እንደው ከንቱ ውሽልሽል የተለጣጠፈ።
ሕዝብ እንዴት ይመነው የተሸራረፈ፣
በአንድነት ለአገር በውል ያልከተተ፣
ከሀዲ ውትፍትፍ ብዙ ወሰለተ፣
መነጋገርና መወያየት መልካም፣
ለሕዝብ ደህንነት ታሪክ በማስቀደም፣
አገርን ለማዳን ሰላምን ለማምጣት በአንድነት ለማለም።

ሕዝብም ያመነበት ስሜቱን የነካ፣
በቋንቋ፣ በጎሣ ድርጅት ያለካ፣
አንድ ሆኖ መስርቶ ሁለት ሦሥት ያልሆኑ፣
አቻነትን በአለው የተመጣጠኑ፣
ለአንድ አገር ኢትዮጵያ ከልብ ያመኑ፣
ኢትዮጵያዊነትን ለትውልድ ያሰቡ፣
በቁርጥ በፅናት በአቻነት ቢቀርቡ፣
ይሆን ነበር ውሉ የሰመረ ሕብረት፣
ለአገር ነፃነት ለሕዝብ እኩልነት፣
ለአገር ለወገን ካልሆነ በፍቅር፣
ድርና ማግ ሆኖ ካልሰራ ትብብር፣
ብትን ነጠላ ነው ተለያይቶ የሚቀር፣
መሪ አቋም የሌለው ግብስብስ ውትርትር፣
ወስላታ ውሽልሽል የተገረደፈ፣
ከንቱ ውትፍትፍ ነው ያልተደጋገፈ።